| | |
|---|---|
| ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ | ዙልሒጃህ 1/1440 ሂ. |
| አውቃፍ ሚኒስትር | ኦገስት 2/2019 ግ. |

اغتنام مواسم الطاعات والخيرات

## የኢባዳዎችና የበጎ ሥራዎችን ወረቶች አጋጣሚ በሚገባ መጠቀም

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{وَسَارِعُوا إِلَى مَغْفِرَةٍ مِّن رَّبِّكُمْ وَجَنَّةٍ عَرْضُهَا السَّمَاوَاتُ وَالأَرْضُ أُعِدَّتْ لِلْمُتَّقِينَ * الَّذِينَ يُنفِقُونَ فِي السَّرَّاءِ وَالضَّرَّاءِ وَالْكَاظِمِينَ الْغَيْظَ وَالْعَافِينَ عَنِ النَّاسِ وَاللَّهُ يُحِبُّ الْمُحْسِنِينَ}

ለአለው ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (ከጌታችሁ ወደ ኾነችም ምሕረትና ስፋትዋ እንደ ሰማያትና ምድር ወደ ኾነች ገነት አላህን ለሚፈሩ የተዘጋጀች ስትኾን ተቻኮሉ፡፡ ለእነዚያ በድሎትም ኾነ በችግር ለሚለግሱት፣ ቁጭትንም ገቺዎች ከሰዎችም ይቅርታ አድራጊዎች ለኾኑት (ተደግሳለች)፡፡ አላህም በጎ ሠሪዎችን ይወዳል፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም በተከበረው ሓዲሳቸው (አንድም በአላህ ባሮች ላይ የሚነጋ ሌሊት የለም ሁለት መልኣኮች ወርደው አንደኛው ፡ ጌታዬ ሆይ ለጋሽን ሰው በለገሰው ነገር ምትክ ስጠው ሌላኛው ደግሞ ጌታዬ ሆይ ግነዘቡን ጨምድዶ ያዘን ሰው ጥፋትን ፍረድበት የሚሉ ቢሆን እንጂ)፡፡ ያሉት ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

አላህ (ዐ.ወ.)ባሮቹ ዘወትር ወደሱ ለመቃረብ እንድጥሩና ወደሱ መዞራቸውንም እንዲያሳምሩ ለመገፋፋት ከዘመን ቀናት የመልካም ሥራ ምንዳ እጥፍ ድርብ የሚሆኑባቸው፣ በጎ ነገሮች የሚበዙባቸውና ደረጃዎች ከፍ የሚሉባቸው ወራቶችን በመለየት አስቀምጧል፡፡ ልበኛ ሰው ሊባል የሚገባው የነዚህን ወራቶች መልካም አጋጣሚ በሚገባ ለመጠቀም ሀሳብን ያጠራ፣ በነሱም ሥራውን ያሳመረ፣ ወደጌታው አላህ (ዐ.ወ.) በመመለስ በጎሥራዎችን ያበረከተና የአላህ እዝነትና ርህራሄ ለማግኘት ጥረት የሚያደርግ ሰው ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ለጌታችሁ በዘመናችሁ ቀናት የእዝነት ጊዚያት አሉት፡፡ እነሱንም ለማግኘት ጥረት አድርጉ፡፡ ምናልባትም አንዳችሁ ከነሱ አንድ ጊዜ እዝነት ያጋጥመውና ከሱ በኋላ መንጊዜም መናጢነት የሚባል ነገር ላያጋጥው ይችላልና፡፡)

እነዚህ አሁን ያለነባቸው ቀናት መንዳቸው እጅግ ታላቅና ደረጃው በጣም ከፍተኛ ከሆኑት የመልካም ሥራ ወራቶች በመጀመሪያ የሚጠቁሱት መሆናቸው ጥርጥር የሌለበት ጉዳይ ነው፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) በነዚህ ቀናት የሚፈጸሙ ዒባዳዎች ከነሱ ሌላ ባሉ ቀናት ከሚከናወኑት በሰፊው እንድበልጡ አድርጓል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) ይህን ወቅት ቀናቱን የተከበሩና ጊዚያቱንም የላቁ አድርጓል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አላህ (ሱ.ወ.) የነዚህን ቀናት ትሩፋትና ታላቅ ደረጃቸውን በተከበረው መጸሐፉ የማለባቸው በመሆኑ ገልጾልናል ሲሉ ማብራራታቸውን ሊቃውንት ጠቁመዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَالْفَجْرِ * وَلَيَالٍ عَشْرٍ * والشفع والوتر}

ትርጉሙም (በጎህ እምላለሁ፡፡ በዐሥር ሌሊቶችም፡፡ በጥንዱም በነጠላውም፡፡) ማለት ነው፡፡

ብዙኃን የቅዱስ ቁርኣን ተንታኞች ዐሥር ሌሊቶች የተባሉት የዙልሒጃ መጀመሪያ ዐሥር ቀናት በመሆናቸው አንድ አቋም ወስደዋል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) ደግሞ በታለቅ ነገር እንጂ የመሃላ ቃል አያሰፍርም፡፡ በነዚህ ቀናት የመሃላ ቃል ማስፈሩም የተከበሩ መሆናቸውንና ደረጃቸው የላቀ መሆኑን ለመግለጽ፣ በላጭነታቸውን ለማብራራትና አበይትነታቸውን ለመጠቆም ነው፡፡ ከነዚህ ቀናት ትሩፋት መካከል አላህ (ዐ.ወ.) የታወቁ ቀናት ሲል የገለጻቸው መሆኑን ነው፡፡ አላህ እንድህ ይላል፡

{وَيَذْكُرُوا اسْمَ اللَّهِ فِي أَيَّامٍ مَعْلُومَاتٍ عَلَى مَا رَزَقَهُمْ مِنْ بَهِيمَةِ الْأَنْعَامِ}

ትርጉሙም (ለእነሱ የሆኑ ጥቅሞችን ይጣዱ ዘንድ በታወቁ ቀኖችም ውስጥ ከለማዳ እንስሳዎች በሰጣቸው ሲሳይ ላይ የአላህን ስም ያወሱ ዘንድ (ይመጡሃል)) ማለት ነው፡፡ በነዚህ ቀናት ለማንኛውም ሙስሊም እንደ ስግደት፣ መጽዋት፣ ጾምና ሓጅ ያሉ ተላላቅ ዒባዳዎች የሚካተቱ ሲሆን ከነሱ ሌላ ባሉ ቀናት በእንድ ላይ አይሰባሰቡም፡፡

ከነዚህ ቀናት ትሩፋት ሌላው ደግሞ አላህ የሚወዳቸው ቃናት መሆናቸውና በጎ ሥራም ከነሱ ሌላ ካሉት ቀናት በጎ ሥራዎች የበለጠ አላህ (ዐ.ወ.) ዘንድ የተወደዱ መሆናቸው ሲሆን እነሱም የትርፍ ወራት፣ የስኬት ጎዳናና የበጎ ሥራ መሽቀዳደሚያ አደባባይ ናቸው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ከነዚህ ቀናት  የበለጠ በነሱ መልከም ሥራ አላህ ዘንድ አጅግ የሚወደድባቸው ቀናት የሉም፡፡) የዙል ሒጃ ዐሥር ቀናትን ማለታቸው ነበር፡፡ ያን ጊዜም ባልደረቦች  የአላህ መልክተኛ ሆይ! በአላህ መንገድ ከመወጋትም? በማለት ጠየቁ፡፡ እሳቸውም (-አዎ- በአላህ መንገድ ከመዋጋትም አንድ ገንዘቡንና ሕይወቱን ሰዉቶ የወጣና ከነሱም በምንም ያልተመለሰ ሰው ሲቀር፡፡) በማለት መለሱ፡፡ በመሆኑም ማነኛውም ሙስሊም በተለያዩ የዒባዳ ዓይነቶች ወደአላህ (ዐ.ወ.) በመቃረብ የዚህን ታላቅ ትርፍና ሰፊ ምንዳ መልካም አጋጣሚ በተገቢው መልኩ ሊጠቀምበት ይገባል፡፡

በነዚህ ቀናት የአላህ ባሮች ወደአላህ (ዐ.ወ.)ሊቃረቢባቸው ከሚችሉ ዒባዳዎች መካከል የገንዘብና የአካል አቅም ለአለው ሰው የሓጅን ሥራ ማድረሱ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{ٱلْحَجُّ أَشْهُرٌ مَعْلُومَاتٌ فَمَنْ فَرَضَ فِيهِنَّ ٱلْحَجَّ فَلَا رَفَثَ وَلَا فُسُوقَ وَلَا جِدَالَ فِي ٱلْحَجِّ}

ትርጉሙም (ሐጅ (ጊዜያቱ) የታወቁ ወሮች ናቸው:: በእነርሱም ውስጥ ሐጅን (እንዲሠራ) ነፍሱን ያስገደደ ሰው በሐጅ ውስጥ ሴትን መገናኘት ማመጽም ክርክርም የለም::) ማለት ነው:: ሐጅን ማድረስ ከእስልምና ማእዘናት አምስተኛው ማእዘን መሆኑ ይታወቃል:: በሱም ነገሮች ይሟላሉ፣ ኃጢአቶች ይማራሉ አንድሁም በነሱ ለአንድ የአላህ ባሪያ አድስ ልደት ይከተብለታል:: ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ሴትን መገናኘትና ማመጸንም ሳይፈጽም ሐጅን የሰራ ሰው እናቱ እንደወለደችው ቀን ሆኖ ይመለሳል::)

ሐጅ ትሩፋትንና የላቀ ሥነ መግባርን ለመማር ታላቅ አጋጣሚ ነው:: በዚህ አጋጣሚ አንድ ሙስሊም በአላህ ፍራቻ ይታነጻል፣ የመንፈሱን ተፈጥሯዊ ፍላጎትና ስሜቷን መቆጣጠርም ይችላል:: እንደከራስ ሰዎችን ማስቀደም፣ ጥብቅነትና ከውርደት መራቅን የመሳሰሉ ሥነ ምግባርን ይማራል:: እንዲሁም በዚህ አጋጣሚ አንድ ሙስሊም በስራና በቃል ጥንቁቅነትና ሥነ ስርኣትን ይማራል:: አንድ የሀጅን ሥራ የጀመረ ሰው የሐጅ ሥነ መግባራዊና ስርኣዊ ይዘቶቹ እንዲሚሉለት የአስልምና እምነት መሰረታዊ መመሪያ የሆኑትን እሴቶችና ሥነ ምግባርት እውን ማድርግ ይጠበቅበታል::

እዚህ ላይ ልናረጋግጠው የሚገባ ነገር ቢኖር የሐጅ ዒባዳ ለአለም ሁሉ የሚተላለፍ የሠላም መልእክት መሆኑን ነው:: ሐጅ በአጠቃላይ መልኩ ጸጥታን፣ ሰላምንና ደህንነትን ያቀፈ ዒባዳ ነው:: አንድ የሀጅን ሥራ የጀመረ ሰው አይጠቃጨቅም፣ አይከራከርም፣ አውሬንም አንድደነብር አያደርግም:: አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لا تَقْتُلُوا الصَّيْدَ وَأَنْتُمْ حُرُمٌ}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እናንት በሐጅ ሥራ ውስጥ ስትኾኑ አውሬን አትግደሉ::) ማለት ነው::

በነዚህ ቀናትና በዚህ ቦታ የሰው ልጅ ሰላም እንሰሳትንም አልፎ እጽዋትንም ያካትታል:: አንድ በሐጅ ሥራ ውስጥ ያለ ሰው ከእጽዋትም ጋር ሰላም እንድፈጥር ተዟል:: ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አላህ (ዐ.ወ.) ይህን ሀገር እርም አድርጎታል:: እሾኩ አይቆረጥም፣ በአውሬውም ጉዳት መድረስ አይፈቀደም:: እንድህም ወድቆ የተገነ ነገር ባለቤቱን ለማፈላለግ እንጂ አይነሳም::) ይህም ለአንድ ሙስሊም ከሐጅ ከተመለሰ በኋላ በሰዎች፣ በዛፍና በደንጋይም ላይ ተንኮል እንዳይፈጽም ልዮ ግንዛቤ እንድቀስም ያደርጋል::

እውነተኛ ሙስሊም ማለት የሰው ልጅ ከምላሱም ሆነ ከእጁ ተንኮል የዳነ ሰው ነው:: ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በመጨረሻ በአደረጉት ድስኩር እንድህ ይላሉ፡ (ንቁ ሙእሚን ማለት ማን እንደሆነ ልንገራችሁን? ሰዎች በገንዘባቸውና በሕይወታቸው እምነት የጣለቡት ሰው ነው:: ሙስሊም ማለት ደግሞ በሰዎች ላይ በምላሱም ሆነ በእጁ ተንኮል የማይፈጽም ሰው ነው:: የሃማኖት ተጋዳይ ማለት ደግሞ ለአላህ ታዛዥ እንድትሆን መንፈሱን ተጋድሎ ያሸነፈ ሰው ነው:: የሃይማኖት ስደተኛ ማለት ደግሞ ኃጢአትና ወንጀልን የተወ ሰው ነው::)

አንድ የአላህ ባሪያ ወደጌታው ከሚቃረብባቸው በላጭ ሥራዎች መካከል በነዚህ የተባረኩ ቀናት ጾምን መጾም ይካተታል፡፡ ጾም ከበላጭ ዒባዳዎችና ከአላህ መቃረቢያ ታላቅ ዒባዳዎች አንዱ ነው፡፡ የጾም ደረጃ ከፍተኛ በመሆኑ አላህ (ሱ.ወ.) የራሱ እንድሆነ ገልጧል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በተናገሩት የቁድስ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ብሏል፡ (የአደም ልጅ ሥራ ሁሉ የራሱ ነው፡፡ ከጾም በስተቀር፡ ፡ እሱማ የኔ ነው እኔ በሱ ባሪያን እመነዳለሁ፡፡) እንድሁም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (በአልህ መንገድ አንድን ቀን የጾመ ሰው አላህ (ሱ.ወ.) ከፊቱና ከገሀነም መካከል የሰባ ወራት ጉዞ እርቀት ያህል ያራርቃል፡፡) በመሆኑም አንድ ሙስሊም በነዚህ በዘጡኙ የዙልሒጃ መጀመሪያ ቀናት የተቻለውን ያህል ሊጾም ይገባል፡፡ በተለይም ደግሞ የሐጅ ሥራ ላልያዝ ሰው የዐረፋን ቀን መጾም በጣም የተወደደ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (የዐረፋን ቀን መጾም አላህ አንድ ያለፈውን አንድ ዓመትና የቀጣዩን አንድ ዓመት ወንጀል እንደሚያስምር ተስፋ ይደረጋል፡፡)

የዐረፋ ቀን አላህ (ዐ.ወ.) በባሮቹ ላይ እዝነት፣ ምህረትና ከእሳት ነፃነት መሆንን የሚቸርበት ታላቅ ቀን ነው፡፡ በዚህ ቀን አላህ ጸሎትን ይቀበላል፡፡ ለስህተቶችም ምህረት ያደርጋል፡፡ በዚህ ቀን አላህ በምድር ነዋሪዎች ያለውን ኩራት ለሰማያት ነዋሪዎች ይነግራል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ከዐረፋ ቀን የበለጠ አላህ ባሪን ከእሳት ነፃ የሚያደርግበት አንድም ቀን የለም፡፡ እሱም ይቀርብና -በእዝነቱ- በነሱም በመልኣኮች ላይ ይፎክራል፡፡) ይህ ቀን አላህ በሱ እምነትን ምሉእ እንድሁም ተድላን የተሟላ ያደረገበት ቀን ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ለኡመር ኢብን አልኸጣብ ከእለታትአንድ ቀን አንድ አይሁድ እንድህ አላቸው፡ ‹የምእምናን አዛዥ ሆይ! አንድት አንቀጽ በመጸሐፋችሁ የምታነቧት አለች፡፡ በኛ በአይሁዳዊያን ላይ ብትወርድ ኖሮ ያን የወረደችበትን ቅን የሚከበር በአል ባደረግነው ነበር፡፡› እሳቸውም የትኛዋን አንቀጽ ማለትህ ነው? በማለት ጠየቁት፡፡ እሱም አንድህ የምተለውን አንቀጽ ማለቴ ነው አለ፡

{اَلْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ الْإِسْلَامَ دِينًا}

ትርጉሙም (ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ፡፡ ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ፡፡ ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፡፡) ማለትነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዑመር ኢብን አለ ኸጣብ (ያነን ቀን በነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ላይ የወረደችበትንም ቦታ አውቀነዋል፡፡ እሱም በዐረፋ ቁመው እያሉ ዓርብ ቀን ነበር፡ ፡) አሉ፡፡

ማንኛውም ሙስሊም በነዚህ ቀናት አላህ (ዐ.ወ.)ን በሰፊው ሊያወሳ ይገባል፡፡ አላህን ማውሳት የልብ ሕይወት ሲሆን በሱም እርጋታ ይገኛል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{الَّذِينَ آمَنُوا وَتَطْمَئِنُّ قُلُوبُهُمْ بِذِكْرِ اللَّهِ أَلَا بِذِكْرِ اللَّهِ تَطْمَئِنُّ الْقُلُوبُ}

ትረጉሙም((እነሱም) እነዚያ ያመኑ ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት የሚረኩ ናቸው፡፡ ንቁ! አላህን በማውሳት ልቦች ይረካሉ፡፡) ነብያችንም እንድህ ይላሉ፡ (ከነዚህ ዐሥር ቀናት የበለጠ አላህ ዘንድ እጅግ ተላላቅ የሆኑ አንድሁም እሱ ዘንድ በነሱ በጎ ሥራ

እጅጉን የተወደደ የሆኑ ቀናት የሉም፡፡ በነሱም ተህሊልን፣ ተክቢርንና ተሕሚድን አብዙ፡፡) ሰይድና ዑመር ሚና ውስጥ በማረፊያ ቦታቸው ተቀምጠው ሲከብሩ በመስጊድና በገበያም ያሉ ሰዎች ይሰሟቸውና አብረዋቸው ሲከብሩ የሚና ክልል በተክቢራ ይናወጥ እንደነበር ተወርቷል፡፡ ኢብን ኡመርም እንደዚሁ ሚና ወስጥ ከስገደት በኋላ፣ በምንጣፉቸው ተኝተውና በሚቀመጡበትና በመሄዱበትም ቦታ ይከብሩ እንደነበር ታውቋል፡፡

በመሆኑም ማንኛውም ሙስሊም በነዚህ ቀናት የአላህን ታላቅነት በመግለጽ ድምጹን ከፍ አድርጎ ተክቢራ ማለት የተወደደ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ንቁ ከስራችሁ ሁሉ የበለጠ የሆነውን፣ በደረጃም ከፍ ያለውን፣ እንጉሳችሁ ዘንድ የጠራ የሆነውን፣ ለናንተም ወርቅና በር ከመለገስም የበለጠ የሆነውን፣ ጠላታቶቻችሁን አግኝታችሁ አንገቶቻቸውን ከመምታትና አንገቶቻችሁን ከሚመቷችሁ የሚበልጠውን ተግባር ልንገራችሁን?) ባልደረቦችም አዎን ይንገሩን አሉ፡፡ እሳቸውም (አላህን (ሱ.ወ.) ማውሳት ነው በማለት መለሱ፡፡ ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ሙዓዝ ኢብን ጀበል እንድህ ብለዋል፡ ‹ለአንድ ሰው አላህ (ዐ.ወ.)ን ከማውሳት በተሻለ መልኩ ከአላህ ቅጣት በከፍተኛ ደረጃ ሊያድነው የሚችል ሥራ የለም፡፡

ይህ ቃሌን ተናገርኩኝ ለኔና ለናንትም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በሰዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

በነዚህ ቀናት እንድ የአላህ ባሪያ ወደጌታው ከሚቃርብባቸው ተላላቅ ሥራዎች አንዱ ኡድሒያ ማረድ ነው፡፡ ኡድሑያ ማረድ ከአላህ (ዐ.ወ.) ሃይማኖት ምልከቶች አንደኛው፣ የኢብራሂማዊ እመነት መለያና የነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ፈለግ ማስረጃ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

(ذَٰلِكَ وَمَنْ يُعَظِّمْ شَعَائِرَ اللَّهِ فَإِنَّهَا مِنْ تَقْوَى الْقُلُوبِ)

ትርጉሙም(ነገሩ) ይህ ነው፡፡ የአላህንም የሃይማኖት ምልክቶች የሚያከብር ሰው እርሷ ከልቦች የኾነች ጥንቃቄ ናት፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ስለኡድሒያ ተጠይቀው መልስ ሲሰጡ እንድ ብለዋል፡ (የአባታችሁ የኢብራሂም ፈለግ ነው፡፡) እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (የሰው ልጅ በነሕር ቀን ከሚሰራቸው መልካም ስራዎች እርድ ከመጣል አላህ ዘንድ እጅግ የተወደደ የለም፡፡ እሱም በትንሳኤ ቀን ከነቀንዱ፣ ከነጸጉሩና ከነሸኮናው ይመጣል፡፡ የእርዱ ደም ከምድር ከማረፉ በፊት አላህ ዘንድ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያርፋልና በመልካም መንፈስ አበርክቱት፡፡)

የኡድሑያ እርድ መፈቃቀር፣ መተዛዘንና ከማህበረሰቡ አባላት መካከል ጠንከራ ትስሰር እንድኖር የሚያደርገው የማህበራዊ ትብብር ገጽታ አንዱ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በህዝቡ ዘንድ ችግር መስፋፋቱን ባዩ ጊዜ እንድህ አሉ፡ (ከናንተ መካከል የኡድሒያ አርድ የጣለ ሰው ከሱ ምንም ነገር እያለ ሦስተኛ ቀን እንዳይነጋበት፡፡) በቀጣዩ ዓመት ሰዎች የአላህ መልክተኛ ሆይ ባለፈው ዓመት እንዳደረግነው

እናደርግን? ሲሉ ጠየቁ፡፡ አሳቸውም (ብሉ ለድሃ ምጽዋትም ስጡ ከፊሉንም አስቀምጡ፡፡ በዚያ ዓመት ችግር ነበርና በኡድሒያው ሰዎችን እንድታግዙ አስቤ ነበር፡ ፡) አሉ፡፡
ይህን ማለትም በሀገር ችግር ከሌለና ምግብ በተትረፈረፈ ጊዜ (ብሉ አብሉም ከፊሉንም አስቀምጡ) የሚለው የነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ሐዲስ ተቀዳሚ ሲሆን በሀገር ችግር ሲኖር ደግሞ (ከናንተ መካከል የኡድሒያ እርድ የጣለ ሰው ከእርዱ ምንም ነገር እያለ ሦስተኛ ሌሊት እንዳነጋበት) የሚለው የነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ሐዲስ ተቀዳሚ ይሆናል፡፡
እንደሚታወቀው ኡድሒያ በማረድ እንዲሚረጋገጥ ሁሉ ዋጋውን እርዶ ለሚያከፋፍል ወገን በመስጠትም ይረጋገጣል፡፡ምክኒያቱም የዚህ ዓይነቱ የተደራጀ ከፍል በሚገባ አርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች አንድሁም ከብራቸውን በምንም ዓይነት መልኩ ሳይነካ የሚያደርስ በመሆኑ ጥቅሙ የሰፋ ይሆናል፡፡ ችሎታ ያለው ደግሞ እርዱን በመጣልና ዋጋውንም በመስጠት ለወገኖቹ እርዳታ ቢያበርከት እጅግ የተወደደ ነው፡፡ ማንኛውም ሙስሊም ጥቅማቸው በሁሉም የህበረተሰቡ ክፍል ተደራሽ የሚሆኑ የተለያዩ መልካም ሥራዎችን ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡ አንድ ሰው ምጽዋት በሚሰጥበት ወቅት በድሆችና ችግረኞች ልብ ደስታን የሚፈጥር በመሆኑ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ገፋፍቷል፡
يَ{ أَيُّهَا ٱلَّذِينَ آمَنُوا۟ أَنفِقُوا۟ مِمَّا رَزَقْنَاكُم مِّن قَبْلِ أَن يَأْتِيَ يَوْمٌ لَّا بَيْعٌ فِيهِ وَلَا خُلَّةٌ وَلَا شَفَاعَةٌ وَٱلْكَافِرُونَ هُمُ ٱلظَّالِمُونَ}
ትርጉሙም( እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በርሱ ውስጥ ሽያጭ (መበዠት)፣ ወዳጅነትም፣ ምልጃም የሌለበት ቀን ከመምጣቱ በፊት ከሰጠናችሁ ነገር ለግሱ፡፡ ከሓዲዎችም በዳዮቹ እነርሱ ናቸው፡፡)
ከነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) (ገንዘብ በምንም መልኩ) ምጽዋት በመስተት አይጓደልም) የሚል ሐዲስ ተውረቷል፡፡
እኛ በአሁኑ ወቅት መተጋገዝ፣ መተባበርና የሌሎችን ሁኔታ መረዳት እጅጉን ያስፈልገናል፡፡ ይህውም እንድህ ለሚለው ለነብያችን ቃል ለመታዘዝ ነው፡ (ሙስሊም የሙስሊም ወንድም ነው፡፡ አይበድለውም፣ አሳልፎም አይሰጠውም፡፡ የወንድሙን ጉዳይ ለማውጣት የቆመ ሰው፡፡ አላህ ጉዳዩን ያወጣለታል፡፡ ከአንድ ሙስሊም ጭንቅን ያቃለለ ሰው አላህ ከትንሳኤ ቀን ጭንቀቶች አንዱን ጭንቀት የቃልልለታል፡፡ አንድን ሙስሊም ከመጋለጥ የታቀበ ሰው አላህ በትንሳኤ ቀን አያጋልተውም፡፡) ነብይችን (ሰ.ዐ.ወ.)አንድ ቀን (ማንኛውም ሙስሊም ምጽዋት መስጠት አለበት) አሉ፡ ፡ ባልደረቦችም የአላህ ነብይ ሆይ! ገንዘብ ባይኖረውስ? ሲሉ ጠየቁ፡፡ በእጁ ይስራ ከዚያም ራሱንም ይጥቀሞ ምጽዋትም ይስጥ አሉ፡፡ አነሱም ባያገኝስ? አሉ፡፡ እሳቸውም ባለጉዳይንና የተጨነቅን ይገዝ አሉ፡፡ አነሱም ባይችልስ? አሉ፡፡ እሳቸውም ውለታን ይዋል ተንኮል ከመፈጸምም ይታቀብ ይህ ለሱ ምጽዋቱ ነው አሉ፡፡)
ጌታችን ሆይ አንተን እንድናወሳ፣ እንድናመሰግንና ዒባዳህንም እንድናሳምር አገዘን አሜን፡፡